# □ት ሬ□□ አ ስ ተ □□ር

# ት ሬ ነ □ ሪ ት □ □ □

# DIRE NEGARIT GAZETA

## OF THE DIRE DAWA ADMINISTRATION

4ኛ ዓመት ቁጥር 22
ድሬዳዋ ሚያዝያ 18 ቀን 2004 ዓ.ም.

4th Year No.22
DIRE DAWA APR 26 th ,2012


## አዋጅ ቁጥር 22/2004 ዓ.ም

## የድሬዳዋ አስተዳደር ስፖርት ኮሚሽንን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

ስፖርትን ማስፋፋት ህብረተሰቡን በተለይ የወጣቱን ጤንነት በመጠበቅና አእምሮውን የሚያበለፅግበትን ሁኔታ ለማመቻቸት እንዲሁም በአስተዳደሩ ብሎም በአገር አቀፍ ደረጃ እየተካሄዱ ባሉ ዘርፈ ብዙ የልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርግ ጉልህ ሚና የሚጫወት በመሆኑ

የአገራችንን የስፖርት ፖሊሲና የትኩረት አቅጣጫዎቸ በአስተዳደሩ በውጤታማ መልኩ ለማስፈፀም ህዝባዊ መሠረት ያለው ስፖርት እንዲስፋፋ እና የስፖርት አደረጃጀቶችን መደገፍና ማስተባበር፣ የስፖርት ትምህርትና ስልጠና እንዲሁም ማዘውተሪያና ማበልጸጊያ ማዕከላት እን[illegible] ማፍራትና ማበረታታት አስፈላጊ በመሆኑ፣

## Proclamation No 22/2012

## DIRE DAWA ADMINISTRATION

## SPORT COMMISSION RE ESTABLISHMENT PROCLAMATION

WEREAS the promotion of sports makes significant contributions to communities, especially the youth to maintain healthy physical and brain, and thereby facilitate their active participation in all round development activities of the Administration and the Nation.

WHEREAS it is found necessary to execute the Nation's sports policy and its Main Focuses by promoting community based sports, coordinating and supporting sports

organizations, expanding sports Education and trainings, sport facilities and centers, producing and encouraging outstanding sports persons,

የስፖርት ዘርፉ ልማት ዘለቄታዊነት ያለው የራሱ የገቢ ምንጭ ተፈጥሮለት ከመንግስት ድጎማ ጥገኝነት እንዲላቀቅ ለማስቻል የስፖርትንግድስራዎች(ስፖርት ኮሜርሻላይዜሽን) የሚስፋፉበትን ሁኔታ፣ ማመቻቸት በማስፈለጉ፣

WHEREAS it has become necessary to create sustainable source of income for the sport sector by promoting sport commercialization to create a conducive situation that would facilitate the gradual autonomy of sport by doing away with government subsidy,

የስፖርት ምክር ቤት ህዝባዊ መሠረት ያለው ስፖርት እንዲስፋፋ አስተዳደሩ ለሚያደርገው እንቅስቃሴ ውጤታማነት የማይተካ ሚና ስለሚጫወትበት ሁኔታና በስፖርት ልማቱ የመንግስታዊና ህዝባዊ አደረጃጀቶች እንዲሁም የሚመለከታቸው አካላት ቅንጅታዊ አሰራርን በግልፅ መደንገጉ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

WHEREAS to determinate clearly the remarkable role of the sports council in the effort of the Administration to promote community based sport and to strengthen the coordination of Government and public organizations, and stakeholders for sport development,

የስፖርት ዘርፉ በባህሪው የመንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላትን ሰፊ ተሳትፎና ቅንጅት የሚጠይቅ በመሆኑና እነዚህን ባለድርሻ አካላት አስተባብሮ ቀጣይነት ባለው መልኩ በብቃት የሚመራ የአስተዳደሩ አስፈፃሚ መስሪያ ቤት ማቋቋም በማስፈልጉ፣

WHEREAS the sport sector in its nature requires the mobilization and coordination of Governmental and Non- governmental organization so that it is vital to establish the executive organ of the administration in order to coordinate and lead these organs for executing the sport policy competently,

የድሬዳዋ አስተዳደር ምክር ቤት በድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/1996 ዓ.ም አንቀፅ 12 (1) (ሀ) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን አዋጅ አውጥቷል፡፡

Now, THEREFORE, in accordance with Article 12,(1) (a) of the Dire Dawa Administration charter proclamation No 416.2004, the Dire Dawa Administration Council is hereby proclaim as follows,

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ " የድሬዳዋ አስተዳደር ስፖርት ኮሚሽን  ማቋቋሚ አዋጅ ቁጥር 22 / 2004 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል"፡፡

### 2. ትርጓሜ.

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያስጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "ኮሚሽን" ማለት የድሬዳዋ አስተዳደር ስፖርት ኮሚሽን ነው፡፡
2. "አዋጅ" ማለት የድሬዳዋ አስተዳደር ስፖርት ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ነው፡፡
3. "አስተዳደር" የድሬዳዋ አስተዳደር ነው፡፡
4. "ምክር ቤት" የአስተዳደሩ ስፖርት ም/ቤት ነው፡፡
5. " የስራ አስፈፃሚ ቦርድ" ማለት  የምክር ቤቱን ውሳኔዎችና መመሪያዎች የሚያስፈፅም አካል ነው፡፡
6. "የስፖርት ማህበር" ማለት  በድሬዳዋ አስተዳደር ስፖርት

## PART ONE

## GENERAL

### 1- SHORT TITLE

This proclamation may be cited as ''the Dire Dawa Administration sport commission Establishment proclamation No 22 /2012''

### 2- Definition

In this proclamation, unless the context requires other wise

1. ''Commission'' means Dire Dawa Administration sport Commission
2. ''proclamation'' means Dire Dawa administration Sport Commission Establishment Proclamation No---/2011
3. ''Administration'' means Dire Dawa Administration.
4. ''Council'' means Dire Dawa Administration sport council
5. '' Executive Board'' means an organ that implements the decisions and directions of the council effectively
6. ''Sport Associations'' means Association established in Dire Dawa

ኮሚሽን ፈቃድ አግኝቶ የተቋቋመ የስፖርት ፌዴሬሽን፣ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ፣ የአስተዳደሩ የከፍተኛ ት/ት ተቋማት ስፖርት ማህበር፣ የስፖርት አሶሴሽን፣ የድሬዳዋ ኢንተርናሽናል ቴኳንዶ አሶሴሽን፣ የስፖርት ለሁሉም ኮሚቴ እና የስፖርት ክለቦች እና ሌሎች የሚቋቋሙ የስፖርት ማህብራትን ያካትታል፡፡

7. "የስፖርት ፌዴሬሽን" ማለት አንድን የስፖርት አይነት በአስተዳደሩ ውስጥ ለማስፋፋትና ለመምራት ከስፖርት ኮሚሽን ፈቃድ የተሰጠው አካል ነው፡፡

8. "የማህበረሰብ ስፖርት ኮሚቴ" ማለት በስፖርት ፖሊሲው የትኩረት አቅጣጫ መሠረት በገጠርና በከተማ ቀበሌዎች ስፖርትን ለማስፋፋትና ለመምራት የተቋቋመ ኮሚቴ ነው፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን፣

ይህ አዋጅ ተፈፃሚ የሚሆነው በድሬዳዋ አስተዳደር ስፖርት ኮሚሽን፣የስፖርት ምክር ቤትና በሌሎች የስፖርት ፖሊሲው አስፈፃሚ አካላት ላይ ይሆናል፡፡

## 4. የኮሚሽኑ ዓላማ፣

1. ህዝባዊ መሠረት ያለው ስፖርት እንዲስፋፋ ማድረግ፣
2. የስፖርት አደረጃጀቶችን መደገፍና ማስተባበር፣
3. የስፖርት ትምህርትና ስልጠናና ማዘውተሪያዎችን ማስፋፋት
4. ምርጥ ስፖርተኞችን ማፍራትና ማበረታታት፣

Administration and get license from the sport commission including sport Federation, Paralympics committee, Higher Education institution sport associations, Dire Dawa International Tiquando Association, Sport for all committee, sport clubs and other related association,

7. ''Sport federation'' means Federation established in a certain type of sport and authorizes to promote and direct such sport.

8. ''Community sport committee'' means committees established at urban and rural kebeles to promote and direct sports based on the Main Focus of the Sport Policy

## 3. Scope of Application.

This proclamation shall be applicable on Dire Dawa Administration sport commission and sport council, and also on other organs for the execution of the sport policy.

## 4. 0bjective of the commission.

1. promote community based sports,
2. organize and support sport organizations

3. cause the expansion of sport facilities, Education and Trainings,
4. cause to produce and encourage outstanding sports persons.

5. መቋቋም

1. የድሬዳዋ አስተዳደር ስፖርት ኮሚሽን (ከዚህ በኋላ "ኮሚሽን" ተብሎ የሚጠራው) ራሱን የቻለ ህጋዊ ሰውነት ያለው አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት ተቋቁሟል፣
2. የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለአስተዳደሩ ከንቲባ ይሆናል

**ክፍል ሁለት**

**ስለኮሚሽኑ አደረጃጀት፣የኮሚሽኑና የኮሚሽነሩ ስልጣንና ተግባር**

6. የኮሚሽኑ አደረጃጀት

ኮሚሽኑ የስፖርት ም/ቤት፤ በከንቲባው የሚሾም ኮሚሽነር እና አስፈላጊ የስራ ክፍሎች፤ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

7. የኮሚሽኑ ስልጣንና ተግባር

1. ሀገራዊ የስፖርት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፣ ያስደርጋል፣ አፈፃጸሙን ይከታተላል፣
2. በአስተዳደሩ ለሚንቀሳቀሱ የስፖርት ማህበራትና የስፖርት ስልጠና ማዕከላት ፈቃድ ይሰጣል፣ ይመዘግባል፣ ይሰርዛል፣ ፕሮግራማቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣
3. በአስተዳደሩ የስፖርት ማህበራት ማቋቋሚያ መመሪያ ያወጣል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣

**5. Establishment**

1. **Dire Dawa** Administration sport commission (herein after called ''the commission'') is hereby established under this proclamation as an autonomous executive organ of the administration having its own legal personality.
2. The Accountability of the commission shall be to the Mayor.

**PART TWO**

**Organization of the Commission and POWER and FUNCTON OF THE COMMISSION AND COMMISSIONER**

**6. Organization of the Commission**

The commission shall have the sport council, a commissioner appointed by the Mayor, the necessary job departments, coordinators and workers

**7. Power and function of the commission**

1. Execute, cause to be executed and follow up the implementation of strategies, and sport policy of the country,
2. Issue license, register, supervise, as the case may be necessary revoke license and follow up the programs of sport associations and sport training centers of the administration.

11. Provide facilities for the production of sports materials and equipments in the administration,
12. Coordinate the relations with governmental and non-governmental organizations regarding sports Affairs;

13. የንግድ ስራ ፈቃድን በተመለከተ ለሌሎች አካላት በህግ የተሰጠው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የስፖርት ማህበራት ልዩ ልዩ ገቢዎችን ለማመንጨት የሚያስችል ከዓላማቸው ጋር ተዛማጅነት ያላቸው የንግድ ስራዎች ላይ እንዲሳተፉ ይፈቅዳል፣ ይከታተላል ;ደጋፍ ያደርጋል፡፡

14. ለፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን የተሰጠው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የስፖርት ህክምና አገልግሎት ከሚመለከታቸው ጋር በመቀናጀት ያደራጃል፣አገልግሎቱ እንዲስፋፋ ያመቻቻል፣ በስፖርት አበረታች መድሃኒቶችና እፆችን መጠቀምን ለመከላከል በአገር አቀፍ ደረጃ የሚዘረጋውን ስርዓት ያስፈፅማል፣

15. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል

## 8. <u>የኮሚሽነሩ ሥልጣንና ተግባር፣</u>

1. የኮሚሽኑ ዋና ስራ አስፈፃሚ በመሆን የኮሚሽኑን ስራዎች በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ያስተባብራል፣

2. ከላይ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) በአጠቃላይ አነጋገር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነሩ

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀፅ 7 የተዘረዘሩትን የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባሮች ሥራ ላይ ያውላል ስለመዋላቸውም ይከታተላል፡፡

13. Without prejudice to the power vested with other organs to Issue Business license in accordance with the law, authorize and follow up sport associations to engage in income generating activities which are consistent with their objective with a view to meet their financial requirements,

14. Without prejudice to the power vested with Federal sport commission, Follow up and ensure the organization of sport medical facilities in coordination with the concerned Organs; and the adoption of systems for controlling doping practices Nationally,

15. Carry out other activities, to meet its objectives

## 8. <u>Power and function of the commissioner</u>

1. The commissioner shall be the chief executive officer of the commission and as such, shall direct and administer all the activities of the commission.
2. Without limiting the generality stated in sub-article(1) of this Article, the commissioner shall,
   a) Exercise the powers and functions of the commission specified in Article 7 of this Proclamation.

ለ) የኮሚሽኑ የሥራ ፕሮግራሞች እና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ስራ ላይ ያውላል፣

ሐ) ለኮሚሽኑ በተፈቀደው በጀት እና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደረጋል፣

መ) ኮሚሽኑ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርገው ግንኙነቶች ሁሉ የኮሚሽኑ ህጋዊ ተወካይ ይሆናል፡፡

ሠ) የኮሚሽኑን የሥራ አፈፃፀም እና የሂሣብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለአስተዳደሩና ለሚመለከተው አካላት በየጊዜው ይልካል፣

ረ) በአስተዳደሩ ሲቪል ሰርቪስ ህጎች መሠረት የኮሚሽኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳ ደራል፣ ያሰናብታል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የስፖርት ምክር ቤት

### 9. የምክር ቤቱ መቋቋም፣ስልጣንና ተግባር፣

የድሬዳዋ አስተዳደር ስፖርት ምክር ቤት የአስተዳደሩን ስፖርት በበላይነት የሚመራና የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ ከዚህ በኃላ “ምክር ቤት” እየተባለ የሚጠራ አካል በዚህ አዋጅ የተቋቋመ ሲሆን ቀጥሎ የተዘረዘሩት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

b) Prepare the work programs and budget of the commission and implement same upon approval.

c) Effect expenditure in accordance with the approved budget and work program of the commission,

d) Represent the commission in all its dealings with third parties

e) Submit work performance and audit reports of the commission to the concerned organs.

f) Employ and administer, and also dismiss if necessary, employees of the commission in accordance with the civil servants laws of the Administration.

## PART THREE

## SPORT COUNCIL

### 9. establishment; power and Function of the council

Dire Dawa Administration sport council (here in after called “sport council” is hereby established under this proclamation as the Upper leading and decision making organ of Sports and it shall have the following powers and duties:-

1. በስፖርት ዕድገት መሠረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በመምከር የውሣኔ ሃሣብና የስፖርት ፖሊሲ ማሻሻያ ሃሳብ ያቀርባል፡፡
2. በስፖርት ፖሊሲው የትኩረት አቅጣጫዎች መሠረት ስፖርት በቀበሌዎች፣ በት/ቤቶች፣ በስፖርት ማህበራት፣ በወታደራዊ ተቋማት መንግሥታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ህብረተሰቡ ተሳታፊና ተጠቃሚ ስለሚሆንበት፣ ስለሚስፋፋበትና ስለሚለማበት ሁኔታ ይመክራል፣ ሃሣብ ያቀርባል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፡፡
3. ምክር ቤቱ የሚመራባቸውን የስፖርት ደንቦች፣ መመሪያዎችንና ማንዋሎችን ያፀድቃል፣ ያሻሽላል፣ አፋፀማቸውንም ይከታተላል፡፡
4. የስፖርት ምክር ,ቤቱን ዕቅድና በጀት ያፀድቃል፣ ሥራው በዕቅዱ መሠረት መከናወኑንም ይከታተላል፡፡ የሥራ አስፈጻሚ ቦርድና የኦዲት ኮሚቴዎችን የአፈፃፀም ሪፖርት ያዳምጣል፣ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
5. በህግ መሠረት የአስተዳደሩን የስፖርት ልማት ፈንድ ያቋቁማል፣ ያስተዳደራል፣ ቋሚ የገቢ ምንጭ የሚፈጠርበትን ስልት በመቀየስ ተግባራዊ ያደርጋል፣
6. የስፖርት ገቢና ለስፖረት የሚሰጥ ዕርዳታ ከማንኛውም ግብር ነፃ የሚሆንበትን ሁኔታ ይመክራል፣ ለሚመለከተው አካልም ያቀርባል፣

(1) Deliberate on and forward recommendations and proposal on sport development and amendment of policy issues

(2) Based on the Main Focus of the sport policy, forward advice and proposal prompting sports in kebeles, schools sport Associations, Military institutions, Government and NGO's and, also enable the public to participate in and benefit from It; follow up its implementation

.

3. Approves and amend sport Regulation directives and Manual, and follow up their implementation.
4. Approves its work plan and budget; follow up, hear the performance and Audit reports of the Executive Board and Audit Committee, pass decision on the report.
5. Establish and administer the Sport Dvelopment Fund in the administration based on the concerned laws; devise and implement mechanisms create permanent sources of income.
6. Advice and forward recommendations about the mechanism exempting sport incomes and donations from any tax

7. የምክር ቤቱን የክብር አባላት ይሰይማል፡፡
8. የምክር ቤቱን የሥራ አስፈፃሚና ቦርድና የኦዲት ኮሚቴን ይመርጣል፣ ይሽራል፣
9. በስፖርት ማህበራት መካከል ለሚፈጠሩ አለመግባባቶች ውሣኔ ይሰጣል፣
10. የምክር ቤቱን ደንቦችና መመሪያዎች በሚጥሱ የምክር ቤቱ አባሎች፣ አባል ድርጅቶችና የስፖርት ማህበራት ላይ በየደረጃው ዕርምጃ እዲወስድ ያደርጋል፡፡
11. የምክር ቤቱን ገንዘብና ንብረት አላግባብ በሚያባክኑ ወይም ለግል ጥቅማቸው በሚያውሉ የም/ቤቱ አባሎች፣ አባል ድርጅቶች፣ ስፖርት ማህበራትና ግለሰቦች ላይ የሥነ-ሥርዓት እርምጃ ይወስዳል፡፡ ህጋዊ እርምጃም እንዲወሰድባቸው ያደርጋል፡፡
12. ስፖርቶችንና የስፖርት እንቅስቃሴ የሚመለከት አስቸኳይ ሁኔታ በተፈጠረ ጊዜ አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል፡፡

## 10. የምክር ቤቱ አባላት፣

የስፖርት ምክር ቤቱ በአስተዳደሩ ከንቲባ የሚመራ ሲሆን የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1. የአስተዳደሩ ከንቲባ…………………..……..ሰብሳቢ
2. በጠቅላላ ጉባኤ ከምክር ቤቱ የሚመረጥ………………………..…….ም/ሰብሳቢ
3. የስፖርት ከሚሽን ኮሚሽነር.....................ፀሐፊ

7. Assign its members of Honors
8. Elect Executive Board and Audit Committee members
9. Arbitrate those disputes raise between/ among sport Association
10. Cause to take measures against those members, violating regulation and directive.
11. Take or cause to take measures against those members who misuse the finance and property of the council illegally
12. Take all the necessary measures when urgent cases happen in relation to sport activities.

## 9. Member of the council

The sport council shall be chaired by Dire Dawa Administration Mayor composed of the following members:-

1. The Mayor ……………………… Chair person
2. Member elected by General Assembly……………………… V/chair person

3. Sport commission commissioner ……………………………………….Secretary

4. የትምህርትቢሮ……………………………….አባል
5. የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ……..አባል
6. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ……….. አባል
7. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ……..አባል
8. ጤና ቢሮ ………………………………..አባል
9. የሴቶች፣ ወጣቶችና ህፃናት ቢሮ……….. አባል
10. በአስተዳደሩ የተቋቋሙ የስፖርት ማህበራት ፕሬዝዳንቶች……………………………...አባል
11. የከተማ ቀበሌ ማህበረሰብ ስፖርት ኮሚቴ ሰብሳቢዎች … …………………………አባል
12. የገጠር ቀበሌ የማህበረሰብ ስፖርት ኮሚቴ ተወካይ /4/……………………………… አባል
13. የፖሊስ ኮሚሽን ……………………… አባል
14. የአስተዳደሩ ንግድ ኢንዱስትሪና ኢንቨስመንት ቢሮ ……………………………………..አባል
15. የአስተዳደሩ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ……………………………………………አባል
16. የምሥራቅ ኢትዮጵያ ኢሠማኮ ቅ/ጽ/ቤት ……………………………………………አባል
17. ም/ቤቱ የሚያምንባቸው የታወቁ ባለሀብቶች /አምስት ተወካይ / ………………………አባል
18. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ስ/ማህበር ተወካይ ……………………………………………...አባል

4. Education Bureau ………………… Member
5. Government communication affairs Bureau ………………………………………. Member
6. Finance & Economic Development Bureau ………………………………………. Member
7. Urban development and construction Bureau ………………………………………. Member
8. Health Bureau ……………………… Member
9. Women, Children and youth Affairs Bureau ………………………………………. Member
10. Presidents of sport Associations in the Administration ……………………….. Member
11. Chairperson of Urban kebeles Community sport committees …………………….Member
12. Rural kebeles comminute sport committee Representative (4) ……………………Member
13. Dire dawa Police commission ……… ………………………………………..Member
14. Trade, industry and investment Bureau ………………………………………. Member
15. Dire Dawa chamber of commerce ……………………………………… Member

16. Ethiopian Employees Associations confederation Eastern office…………Member

17. Ministry of Defense Dire Dawa representative ……………. …………………………..Member

18. Famous inventers concerned for sport 5 representative………………………… Member

19. የአስተዳደሩ የወጣቶች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት……………………………..… አባል

20. በድሬዳዋ የመከላኪያ ሚኒስቴር ተወካይ - አባል

21. የአስተዳደሩ የሴቶች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ……………………………………………አባል

22. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካይ----- ……………………………………………አባል

23. የግብርና ውሀ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ……አባል

24. የድሬዳዋ ብዙሀን መገናኛ ኤጀንሲ………..አባል

## 11. የም/ቤቱ ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት፣

1. የምክር ቤቱ ሰብሳቢ የምክር ቤቱ ህጋዊ ተጠሪ ይሆናል፣
2. የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ በትክክል መዋሉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣
3. ከም/ቤቱ አባላት 1/3ኛው አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራላቸው ከጠየቁ ወይም ሰብሳቢው ሲያምንበት የም/ቤቱ አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ያደርጋል፣
4. የጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎችን ከፀሐፊው ጋር በመሆን ያዘጋጃል፣

## 12.የምክርቤቱአባላትኃላፊነትና ተጠያቂነት፣

1. እያንዳንዱ የም/ቤቱ አባል ም/ቤቱ የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጣ ለማስቻል በከፍተኛ ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት የመንቀሳቀስ ኃላፊነት እና ግዴታ አለበት፣

19. Sport Association of Higher Education Institution representative ……………………..…….. Member
20. Dire Dawa Administration youth Federation president ………………………………. Member
21. Dire Dawa administration women Federation president …………………..……..…….. Member
22. NGO’S representative……………..….……Member
23. Agricultural water mines and Energy bureau--- …………………………………….……… Member
24. Dire Dawa Mass media agency-………..-Member

### 11. duties & responsibilities of the chair person of the council

1. The chair person shall be the legal representative of the council.
2. Follow up, and supervise the execution of power and function of the council.

3. Arrange an urgent meeting of the council when 1/3 of the members request or the chair person himself believe in it
4. Set the Agendas for the General Assembly in consultation with the secretary.

**12- responsibility and accountability of the members**

1. Each member of the council shall have the responsibility & obligation to discharge his/her responsibility with high initiation and commitment.

2. አባላቱ የም/ቤቱን ሥራ በማከናወኑ ሂደት ኃላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው ለሚመጣው ጉዳት በጋራ እና በተናጥል ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡

## 13. ስለም/ቤቱ ስብሰባና የአሰራር ሰርዓት፣

ም/ቤቱ እንቅስቃሴውን ውጤታማ ለማድረግና ወጥ የአሰራር ሰርዓት እንዲሰፍን ለማስቻል የራሱን የስብሰባና የአሰራር ስርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 14. የም/ቤቱ ስራ አስፈፃሚ ቦርድ፣

የስፖርት ም/ቤቱ ውሳኔዎቹንና የሚያስቀምጣቸውን አቅጣጫዎች በቀልጠፋና ውጤታማ ሁኔታ የሚያስፈፅም አባላቱ ከስፖርት ም/ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጡ የስራ አስፈፃሚ ቦርድ ይኖረዋል፡፡ የስራ አስፈፃሚ ቦርዱ አባላት

1. የስፖርት ኮሚሽን ኮሚሽነር.. …….ሰብሳቢ
2. የትምህርት ቢሮ……... …….. ም/ሰብሳቢ
3. የፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር…………. አባል
4. በጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጥ አቃቤ ነዋይ .. …………………………………….አባል
5. ከፌዴሬሽንና አሶሴሽኖች/5 ተወካይ/ … ………………………………….አባል
6. ከታወቀ ድርጅቶችና ባለሀብቶች 1 ተወካይ … …………………………………….አባል
7. የአስተዳደሩ ወጣቶች ፌዴሬሽን ፕሬዚንዳት … …………………………………….አባል

2. The members of the council accountable jointly and severally in failing to bear their responsibilities

## 13. Rules and Meetingprocedures

The Council may declare its rule to regulate activities and meetings procedures.

**14. Executive Board of theCouncil**

For the purpose of executing its decisions, and directions set, executive board of the council its members elected out of the council, shall be established. The members shall consists of;

1. Sport commission commissioner …………………………………. Chairperson
2. Education bureau ……………… V/chairperson

3. Police commission commissioner ……………………………………… Member
4. Finance Affairs (elected by General Assembly) …………………………… Member
5. Federations and Associations representative ……………………………………… Member
6. Famous organizations and investors representative ………………… Member
7. Youth Federation president …… Member
8. ስፖርት የማስፋፋትና የማ/ሥ/ሂ/ተወካይ ……………………………ፀሐፊና አባል

## 15. <u>የስራ አስፈፃሚ ቦርዱ ስልጣንና ተግባር</u>

1. የጠቅላላ ጉባኤው ውሣኔዎች፣ ደንቦችና ልዩ ልዩ መመሪያዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ያስፈፅማል፣
2. ጠቅላላ ጉባኤው በሚያስተላልፈው ውሣዎችና መመሪያዎች መሠረት በስራ ላይ የሚውል ፕሮግራም አዘጋጅቶ ያቀርባል ሲፀድቅ ተከታትሎ ያስፈፅማል፣
3. አስፈላጊ የሆኑ ንኡሳን ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ የሥራ ጊዜያቸውንም ይወስናል ተግባራቸውንና የአሰራር ማኑዋሎች አዘጋጅቶ ለም/ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ ያፀድቃል፡፡
4. የምክር ቤቱን ዓመታዊ ጉባዔ ያዘጋጃል፣
5. ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴና የፋይናንስ ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባዔው ያቀርባል፡፡
6. የምክር ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ ይመራል ይቆጣጠራል፣

8. Sport commissions sport development core process ……………………………. Secretary

## <u>15 power & Function of Executive Board</u>

1. Follow up the implementation of the decisions of the council's General Assembly, Regulations, and various Directives.
2. Based on the decisions and directives of the General Assembly of the council, it shall prepare an enforceable program, implement same upon approval of the council.
3. Establish necessary sub-committees, decide their tenure; prepare their Function and Manuals for the sub committees and provide same for the approval to the General Assembly of the council.
4. Arrange the meetings of General Assembly of the council

5. Submit the annual performance and financial report for the General Assembly.
6. Directs, follow up and, monitor activities of the council.

7. በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡ አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥም ከዚህ ባነሰ ጊዜ ሊሰባሰብ ይችላል፣
8. በተጨማሪም ዓላማውን ከግብ ለማድረስ በጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጡትን ሌሎች ተመሣሣይ ተግባሮች ያከናውናል፡፡

16. **የሥራ አስፈፃሚ ቦርዱ ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት**

1. ሥራ አስፈፃሚ ቦርዱን በሚመለከቱ ጉዳዮች የቦርዱ ተጠሪ ይሆናል፡፡
2. የሥራ አስፈፃሚ ቦርዱንና የአስቸኲዋይ ጊዜ ኮሚቴን ስብሰባ ይመራል፤ድምፅ እኩል ሲሆን ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡
3. የም/ቤቱን ሂሣብ ከኮሚሽኑ ፋይናንስ ግዢና ንብረት አስተዳደር ደጋፊ የሥራ ሂደት መሪ እና ከአቃቤ ንዋዩ ጋር በመሆን ያንቀሳቅሳል፡፡
4. ከፀሐፊው ጋር በመሆን የሥራ አስፈፃሚ ቦርዱን አጀንዳ ያዘጋጃል
5. የስራ አስፈፃሚ ቦርድን ውሳኔዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል፡፡

**17. የቦርዱ ስብሰባ ሥነ- ሥርዓት፣**

ምክር ቤቱ የቦርዱን የስብሰባና የአሰራር ስነ ስርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

7. hold regular meetings per month; provided, however, that it may hold an extraordinary meeting whenever necessary
8. Carry out such other activities provided to it by the General assembly to attain its objectives.

**16. power & function of the Executive Board Chairperson**

1. Represent the executive Board on in dealings concerning it.
2. Directs the meeting of the Executive Board and Emergency committees. decision shall be passed by a majority Vote, however, when votes are in tie, idea supported by the chairperson shall be the decision of the executive Board.
3. Sign on accounts of the council jointly with finance, purchase and property Administration support process head and the responsible person for the finance Affairs of the Council.
4. Prepare Agendas for meetings of the Executive Board in coordination with the secretary of the Board
5. Follow up and supervise the implementation of Board Decisions.

**17. Meeting Procedures of the Board**

The Council shall issue the regulation and Meeting procedures for the Executive Board.

**ክፍል አራት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች፣**

**18. ስለ በጀት ምንጭ፣**

1. የኮሚሽኑ በጀት በአስተዳደሩ /በመንግስት የሚመደብ ይሆናል፣
2. ከአስተዳደሩ ከሚመደበው በጀት በተጨማሪ ኮሚሽኑ ከልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ምንጮች የውስጥ ገቢ መፍጠርና ገቢውንም በአግባቡ ሊጠቀምበት ይችላል፡፡

**19. ስለ ሂሣብ መዝገብ አያያዝና ኦዲት፣**

1. ኮሚሽኑ በፋይናንስ ህግ መሠረት የተሟሉና ትክክለኛ የአሰራር ስርዓትን ተከትለው የተመዘገቡ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፣
2. የኮሚሽኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በአስተዳደሩ ዋናው ኦዲተር እንዲመረመሩ ይደረጋል፡፡

**20. ስለተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች፣**

1. የድሬዳዋ አስተዳደር አስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤታዊ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 16/2003 ዓ.ም አንቀፅ 12 ተሽሮ በዚህ አዋጅ ተተክቷል፡፡
2. ይህ አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ህግ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**PART FOUR**

**MISCELLANEOUS PROVISIONS**

**18. Budget Source**

1. The Administration shall allocate budget of the commission annually.
2. Without prejudice to sub Article (1) of this Article, the Commission may generate its own internal income from different source, and utilize such income properly consistently with its objectives and financial rules and regulations.

**19. Books of Accounts & Audit**

1. The commission shall handle accurate, complete and procedural books of accounts in accordance with financial regulations.
2. Financial records and books of Accounts shall be audited by chief Auditor of the Administration .

**20. repealed and inapplicable laws**

1. Article 12 of the Dire Dawa Administration Executive and Municipality services organs Reestablishment proclamation No 16/2010 is hereby repealed.

2.Any laws and customary practices which are inconsistent with this proclamation shall have of no effect on matters provided for in this proclamation.

## 21. ስለአዋጁ መሻሻል

ይህ አዋጅ አስፈላጊ መሆኑ ሲታመንበት በድሬዳዋ አስተዳደር ምክር ቤት ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 22. ደንብ የማውጣት ስልጣን፣

የአስተዳደሩ ካቢኔ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልግ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 23. ስለመተባበር ግዴታ፣

ማናቸውም መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ለዚህ አዋጅ ስራ ላይ መዋል የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

## 24 ጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በድሬ ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ድሬዳዋ ሚያዚያ 18 ቀን 2004 ዓ.ም**

**አሰድ ዚያድ**

**የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ**

**21. Amendment**

**The Dire Dawa Administration Council may amend this Proclamation when it finds necessary.**

**22. Power to issue regulation.**

The cabinet of Dire Dawa Administration may issue Regulation, where it finds necessary, for the purpose of enforcing this proclamation effectively.

**23. Obligation to cooperate**

Any Government, Non Governmental organizations and concerned organs shall have an obligation to cooperate in enforcing this proclamation.

**24. effective date**

This proclamation shall come into force up on the date of publication in the Dire Negarit Gazeta

**DONE AT DIRE DAWA THIS** APR 26 **DAYS OF 2012**

**ASSED ZIYAD**

**MAYOROFDIREDAWAADMINISTRATIN**